# መመሪያ-ደንብ

## የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

**ተዛማጅ ርእሶች፡-** ACA, ACF, ACF-RA, COG-RA, IGT-RA, JFA, JFA-RA, JGA, JGA-RA, JGA-RB, JGA-RC, JHF, JOA-RA

**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፦** ዋና አካዴሚያዊ መኮንን
የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ

# ተማሪን ማጥቃት፣ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት

I. **ዓላማ**

አካደሚያዊ ግኝት/ስኬት እና ማህበራዊ እድገት የሚገኙፉት ተማሪዎች እና ሰራተኞች ደህንነት ሲሰማቸው መሆኑን የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያምናል። ማሸማቀቅ፣ ማዋከብ፣ ወይም ማስፈራራት የት/ቤቶችን ሰላማዊ የሥራ እንቅስቃሴ ያደናቅፋል። ማሸማቀቅ የሚደርስባቸው ተማሪዎች፣ ሌሎችን የሚያሸማቅቁ ተማሪዎች፣ እና ተመልካቾች የሆኑ ተማሪዎች በተለያየ ደረጃ አስከፊ፣ ሰላም ማጣት፣ እና በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል። ይህ ደንብ በት/ቤቶች ውስጥ ማሸማቀቅ እንዳይደረግ ለመከላከል የሚተገበሩ የመከላከል፣ ቅድመ-ጣልቃ ገብ እርምጃ፣ የመፍትሄ እንቅስቃሴ፣ እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ መዘዙ የሚያስከትለውን ፍቱን እርምጃ፣ እና በዛቻና በጉልበት የሚነዘንዙትን በሚያጋልጡ/በሚጠቁሙ ግለሰቦች ላይ በቀል እንዳይደርስባቸው ጥበቃ የማድረግ ቅደምተከተል ያበስራል።

II. **ፍች/ትርጉም**

A. ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ማለት ሆን ተብሎ የሚደረግ፣ በቃላት፣ በአካል፣ ወይም በፅሁፍ ወይም ሆን ተብሎ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ በመጠቀም በተማሪ የትምህርት ጥቅሞች፣ እድሎች፣ ወይም አፈፃፀም፣ ወይም በተማሪ የአካል ወይም ስነልቦናዊ ደህንነት ላይ ጣልቃ በመግባት ጥላቻ የተሞላበት የትምህርት አካባቢ መፍጠር ማለት ነው እናም፡-

1. ከሁለት አንዱ—

a) በትምህርት ቦርድ መመርያ ACA፣ አድሎ-ያለማድረግ፣ ርትአዊነት፣ ባህላዊ ብቃት ላይ እንደተደገለፀው በተጨባጭ ወይም በይሆናል ግላዊ አስተሳሰብ/ባህሪይ በመገፋፋት፤ ወይም

b) ወሲባዊ ባህርይ ያለው፣ የተማሪን ሃፍረተ ገላ በመግለጽ ዓይነት ወይም የጽሑፍ/ሥዕላዊ መግለጫ ወይም በወሲባዊ ግንኙነት እንደተሳተፉ በማስመሰል አይነት፤ ወይም፣

c) በዛቻ ወይም በከባድ ማስፈራራት፤ እና

2. ወይም ደግሞ—

   a) በት/ቤት ንብረት ላይ፣ በት/ቤት ስፖንሰር በሚደረግ እንቅስቃሴ ወይም ክንውን፣ ወይም በት/ቤት አውቶቡስ ላይ የሚፈፀም፤ ወይም፣

   b) ስርኣት የጠበቀ የት/ቤት ሥራ ክንውን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሰናክል።

B. በኤሌክትሮኒክስ መሳርያ ኣማካይነት/ሳይበርቡሊዩንግ/ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ እና የማስፈራራት ሁኔታ ነው። "ሳይበርቡሊዩንግ" ማለት በኤሌክትሮኒክስ መሳርያ ኣማካይነት የሚተላለፍ መገናኛ ሲሆን በማህበራዊ ሚድያ ጣቢያዎች መገልገልንም ያካትታል። ሳይበርቡሊዩንግ በ"ኤሌክትሮኒክስ መገናኛ" ስር የሚውሉትን ማናቸውንም የወደፊት መተግበሪያዎች/applications ያካትታል።

C. "የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት" ማለት በኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች በመጠቀም የሚተላለፍ ግንኙነት ሲሆን ቴሌፎን/ስልክ፣ ሞባይል ስልክ፣ ኮምፒውተር፣ ወይም ታብሌት ይጨምራል።

D. ጣልቃ-ገብ እንቅስቃሴዎች በድርጊቱ ኣስከፊነት ላይ የተመሰረተ ትኩረት፣ እና ዝውተራ መጠን በተወሰኑ ክስተቶች ኣቅጣጫ የግለሰብ ወይም የኣነስተኛ ቡድን ኣቅርቦቶች ናቸው።

E. ግላዊ ገበና/አካል ማለት፣ በሜሪላንድ የትምህርት ኮድ/Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-424፣ ኮድ ላይ እንደተብራራው እርቃን/የተጋለጠ የወሲብ አካል፣ ብልት አካባቢ፣ ቂጥ፣ ወይም የሴት የጡት ጫፍ ነው።

F. የመከላከል ተግባራት ማለት ማጥቃት፣ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት በብዛት መስፈኑን፣ ምክንያቶችን፣ እና ጎጂ ድርጊት እንደሆነ የጥቃት፣ ማስፈራራት ወይም የትንኮሳ ሠለባ ለሆኑ ወይም ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ ወይም ትንኮሳ ለሚፈጽሙ እና በተመልካችነት ለሚሳተፉ ጭምር የቅን አመለካከት ባህርይ ድጋፍ እና የት/ቤት አካባቢን ለማሻሻል እነርሱንም የሚመለከታቸው አካላት እንደሆኑ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ጠቅላላ ት/ቤት አቀፍ እንቅስቃሴ ማድረግ ነው ።

G. ወሲባዊ ግንኙነት Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-424 ላይ እንደተገለጸው ወሲባዊ ግንኙነት፣ በፍትወተሥጋ(ብልት) ለብልት፣ በአፍና-በብልት ፍትወት መፈጸም፣ ቂጥና-ብልት፣ ወይም ቂጥ በመላስ፣ ከተመሣሣይ ጾታ ጋር ወይም ከተቃራኒ ጾታ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ማለት ነዉ።

## III. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. መከላከል

ሁሉም ት/ቤቶች የመከላከል እና ጣልቃ-ገብነት ስልቶችን እና/ወይም ጎላፊነት የተሞላበት ማህበራዊ እሴቶችን-የሚደግፉ ስነምግባርሮችን የሚያስተምሩና የሚያጠናክሩ እንቅስቃሴዎችን ይተገብራሉ። የሚካተቱት እነዚህ ናቸው፡-

1. ከመከላከል፣ ጣልቃገብነት፣ እና ሙያዊ እድገት ጋር የተያያዙ የአካባቢ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን ለመምራት የት/ቤት አካባቢ ሁኔታ ጥናቶች/ቅኝቶችን መተግበር እና ትንተና ማድረግ።

2. ዓመታዊ የሙያ እድገት እንቅስቃሴዎች ለሁሉም የሰራተኛ ኣባሎች ትኩረታቸው በማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት፣ የማህበራዊ ክህሎት እድገት፣ በት/ቤት የሰላም ኣየር፣ የልዩነቶች መቻቻል፣ ለእድሜ-ኣግባብነት ያላቸው የስነምግባር ሁኔታዎች፣ እና የማሸማቀቅ ተግባሮች ሲከሰቱ የመከላከል ጣልቃ-ገብነቶች ክውነቶች ስልቶች።

3. በትምህርት ዓመት ውስጥ ለተቀጠሩ የሰራተኛ ኣባሎች የተሰጠ ሙያዊ እድገት።

4. የኣወንታዊ ስነምግባራዊ ድጋፎች፣ የጠባይ ትምህርት፣ ሁከት መከላከል፣ እና የት/ቤት መሻሻል በሁሉም ደረጃዎች የስርኣቱ ኣካል በመሆን የተተገበሩ የት/ቤት-ኣቀፍ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት መከላከያ ፕሮግራሞች።

B. ጣልቃ-ገብነት

1. ስለ ማሸማቀቅ መስፋፋት፣ መንስኤዎች፣ እና የመዘዝ ውጤቶች፣ እና ይህን የመከላከል ዘዴዎችን ለማጎልበት ከቤተሰቦችና ከማህበረሰብ ባለጉዳዮች/ባለድርሻ አካላትጋር ትብብር ማድረግ።

2. የማሸማቀቅ ስነምግባሮችን ለሚያሳዩ ተማሪዎች ትምህርት፣ ምክር እና ሌሎች ቀጥተኛ ጣልቃ-ገብነቶች። ጣልቃ-ገብነቶች፣ በነዚህ ሳይወሰን እነዚህን ያካትታሉ፣ መተኪያ ስነምግባሮችና ማህበራዊ ክህሎቶች፣ ራስን-በራስ ማንቃትን ማሳደግ፣ የሰውን ችግር እንደራስ አድርጎ ማየትና ታጋሽነትን ማዳበር፣ እና ለኣይነተ-ብዙህነት ስሜታዊነትና ኣድናቆት።

3. መልሶ-ማቋቋም እና የመፍትሄ ኣቅርቦቶች የማሸማቀቅ ስነምግባርን ለማረም ከቤተሰቦችና ሌሎች የማህበረሰብ ባለጉዳዮች/ባለድርሻ አካላት ጋር የተተለሙ፣ ለራስ ጠበቃ መቆምና በራስ መተማመን የሚረዳ ክህሎት መገንባት፣ የወደፊት ሁኔታዎችን/ክስተቶችን ለመከላከል፣ እና ተጠቂዎችን ከኣፀፋ እና/ወይም ከተጨማሪ የማሸማቀቅ ድርጊቶች መጠበቅ።

4. ተጨማሪ ክስተቶችን ለመከላከል የሚያሸማቅቁ ተማሪዎችን ማህበራዊ-ስሜታዊ፣ ስነምግባራዊ፣ እና ኣካደሚያዊ ፍለጎቶች ለማሟላት ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የጣልቃ-ገብነቶች መስክ።

5. መረጃዎች ለሰራተኛ ኣባሎች፣ ተማሪዎች፣ እና ወላጆች/ኣሳዳጊዎች ስለ ማህበራዊ ኣገልግሎቶች፣ ጤና፣ እና ስነምግባራዊ የጤና መገልገያዎች ከት/ቤት ጣልቃ-ገብነቶች ትግባሬ በኋላ በማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ለመሳተፍ ለሚፀኑ ተማሪዎች እና በማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት እንደ ፈፃሚዎች የሚሳተፉ ተማሪዎች፣ መሸማቀቅ ለደረሰባቸዉ ተማሪዎች፣ወይም ዳር ቁሞ ተመልካቾች የአእምሮ እና የአካል ጤንነት፣ ደህንነት፣ ወይም ኣካደሚያዊ ኣፈፃፀማቸው ላይ ከባድ ተፅእኖ የተደረገባቸው ተማሪዎች።

C. ተከታይ ውጤቶች

1. ኣስቀድመው የማሸማቀቅ ስነምግባሮች ላሳዩ ተማሪዎች የኣወንታዊ ስነምግባራዊ ለውጦች እውቅና፣ ተሸማቀው የነበሩ ኣሁን የማሸማቀቁ ኣድራጎት ያደርሰባቸውን የኣእምሮ መዘባት ለማስወገድ ስልቶችን በመተግበር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች፣ እና ተመልካቾች የነበሩትን ለወደፊት ማሸማቀቅ እንዳይደርስ በመከላከል ንቁ ሚና የወሰዱ ተማሪዎች እውቅና መስጠት።

2. በMCPS የተማሪ ስነምግባር ኮድ መሰረት የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ተግባራት ለሚፈፅሙ ተማሪዎች፣ በብቀላ ወይም ቂም በቀል በተያዙ ተማሪዎች፣ እና/ወይም ሆን ብለው የሃሰት ክስ የመሰረቱ ተማሪዎች የተፈፀሙ ተከታይ ውጤቶች።

3. እያንዳንዱ ት/ቤት፣ በት/ቤቱ ዲሲፕላን ውስጥ፣ ለማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ተግባሮች የተከታይ ውጤቶች ዝርዝር ያካትታል። ተከታይ ውጤቶች ከMCPS ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች፣ የMCPS ደንብ JGA-RB፣ እገዳና መሰናበት፣ የMCPS ደንብ JGA-RC፣ ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች እገዳና ስንብትእና የMCPS የተማሪ ስነምግባር ኮድ መጣጣም አለባቸው።

## IV. የሪፖርት አቀራረብ ሂደቶች

ስለማጥቃት፣ ማሸማቀቅ፣ ወይም ማስፈራራት፣ ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ACF፣ ወሲባዊ ጥቃት/Sexual Harassment እንደተገለጸው፣ የሚከተሉትን ቅደምተከተሎች በመጠቀም ሁነቶች/ክስተቶች ሪፖርት ይደረጋሉ፡-

A. MCPS ፎርም 230-35፣ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ፣ በአንድ ተማሪ ፤ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም የተማሪ የቅርብ ዘመድ፤ ወይም የት/ቤት ሰራተኛ አባል ሊሞላ ይችላል። አንዴ ከተሞላ በኋላ፣ ቅጹ ለት/ቤቱ ርእሰመምህር/ተወካይ ገቢ መደረግ አለበት።

B. አንድ ተማሪ፣ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም የተማሪ የቅርብ ዘመድ ለሰራተኛ አባል በመካሄድ ላይ ያለ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሲያስታውቅ፣ የሰራተኛ አባሉ/ሏ በፍጥነት ጣልቃ ለመግባት ምላሽ ይሰጣል/ትሰጣለች፤ የMCPS ፎርም 230-35፣ ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ቅጽ እንዲሞላ ሃሳብ ያቀርባል/ታቀርባለች፤ አድራጎቱንም ለት/ቤቱ አስተዳዳሪ ወድያውኑ ያስታውቃል/ታስታዉቃለች። ተማሪው/ዋ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጹን በነፃ ካልሞላ/ች ወይም መሙላት ካልፈለገ/ች፣ የሰራተኛ አባል ተማሪው/ዋን፣ ወላጁ(ጇ)ን አሳዳጊው(ዋ)ን፣ የተማሪን የቅርብ ዘመድ ፎርሙን በመሙላት ያግዛል/ታግዛለች።

C. በያንዳንዱ የትምህርት ኣመት መጀመርያ ላይ፣ ርእሰመምህራን ተማሪዎቹን፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን፣ እና ሰራተኞችን ስለ የMCPS ፎርም 230-35፣ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ ፎርም ያስታውቋቸዋል። እያንዳንዱ ት/ቤት የMCPS ቅጽ 230-35 በት/ቤት ጽ/ቤት፣ የኣማካሪ ጽ/ቤት፣ የሚድያ ማእከል፣ እና በጤና ክፍል ይኖረዋል፣ እንዲሁም ቅጹን ለማግኘት በኣካባቢ ት/ቤት ድረ-ገጽ።

## V. የምርመራ ሂደቶች

የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ድርጊቶች ሲመረመሩ የሚከተሉት ሂደቶች ኣገልግሎት ላይ መዋል አለባቸው።

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅጽ/MCPS Form 230-35 ማስጨነቅ፣ ማስገደድ፣ ማስፈራራት፣ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ፣ ለት/ቤት ርዕሰ መምህር/ት እና/ወይም ተወካይ በደረሳቸዉ በሁለት ቀናት ዉስጥ፣በትክክል፣ እና በአጥጋቢ ሁኔታ፣ ሁሉም ወገኖች ማስረጃ እንዲያቀርቡ እድል በመስጠት አስተማማኝ እና የማያዳላ ምርመራ ማካሄድ አለበት/አለባት።

1. ምርመራውን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅጽ/MCPS Form 230-36 ላይ በመሙላት በሠነድ መመዝገብ፣ ማስጨነቅ፣ ማስገደድ፣ወይም የማስፈራራት፣ ሁነት/ክስተት የት/ቤት ምርመራ ቅጽ ላይ መመዝገብ አለበት።

2. የት/ቤት ርእሰ መምህር እና/ወይም ተወካይ ቅጽ/MCPS Form 230-35 በደረሰው/በደረሳት ሦስት ቀኖች ውስጥ በማስፈራራት፣ በማስገደድ፣ በማስጨነቅ ሁኔታ ላይ ተሳትፎ ያደረጉትን ሁሉንም ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ማግኘት አለበት/አለባት።

B. የMCPS ቅጽ 230-35፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ማቅርቢያ ቅጽ፣ እና ኣባሪው የMCPS ቅጽ 230-36፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት የት/ቤት ምርመራ ቅጽ፣ በተማሪ መዛግብት ሚስጢራዊነት ግዴታዎች መሰረት በት/ቤት ጽ/ቤት በሚስጢራዊ ማህደር ውስጥ ይጠበቃሉ። እነዚህ ሰነዶች በተማሪው/ዋ የማጠራቀሚያ ማህደር ውስጥ ኣይካተቱም። ከ 230-35 እና 230-36 ቅጾች የሚገኘው መረጃ/ኢንፎርሜሽን በተደነገገው አሰራር ቅደምተከትል መሠረት OASIS ላይ መካተት አለበት።

C. የት/ቤት አስተዳዳሪዎች እና/ወይም ተወካይ ጣልቃ ገብነቶችን ይተገብራሉ እና/ወይም መፍትሔ ሰጪ እርምጃዎችን እና/ወይም የሚያስከትለውን ውጤት ከሁኔታው/ከክስተቱ ጋር የሚመጣጠን እና ከሥርዓቱ እና በት/ቤት ዲስፕሊን እቅዶችና ቅደምተከተል መሠረት ይተገብራሉ። ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ የመፍትሔ እርምጃዎችን እና የሚያስከትለውን ተጽእኖ በአግባቡ ተግባራዊ ያደርጋል/ታደርጋለች፣ የማስጨነቅ፣ የማስገደድና የማስፈራራት ሁኔታዎች ዳግመኛ እንዳይከሰቱ እርምጃዎችን ይወስዳል/ትወስዳለች ወይም እንደአስፈላጊነቱ ማሸማቀቅ የደረሰበ(ባ)ት ተማሪ ወይም ሌሎች ላይ ያስከተለውን አድሎአዊ ተጽእኖ እንዲታረም ያደርጋል/ታደርጋለች።

D. የት/ቤት ርእሰ መምህር እና/ወይም ተወካይ በማስጭነቅ፣ በማስገደድና ወይም በማስፈራራት፣ ሁኔታ ውስጥ የተሳተፉ የሁሉንም ተማሪዎች ወላጆች እና ሌሎችም የተሳተፉ አካላትን ምርመራው እንደተጠናቀቀ በ 24 ሠዓት ጊዜ ውስጥ መገናኘት አለበት/አለባት።

E. ጥቃት ለፈጸመው/ለፈጸመችው ተማሪ ጥቃት በደረሰበት/በደረሰባት ወይም ተመልካች ተማሪ ላይ ቂም በቀል ወይም የበቀል ርምጃ መውሰድ የተከለከለ እና ሌላ ጥቃት የማድረስ ሁኔታ ከቀጠለ ተጨማሪ የዲስፕሊን እርምጃ እንደሚወሰድ ይገለጽለታል/ይገለጽላታል።

F. ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ በሁለት ሣምንት ውስጥ ኃላፊነት ያለባቸው የት/ቤት ሠራተኞች ጥቃት ከተፈጸመበ(ባ)ት እና ጥቃት ከፈጸመ(ች)ው ተማሪ ጋር ስለ ተፈጸመው ጥቃት፣ ማስገደድ፣ ወይም ማስፈራራት ሁኔታው የረገበ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለየዩ/ለየብቻ ኮንፈረንሶችን ያካሄዳሉ። እነዚህ ስብሰባዎች የምክር ጣልቃ-ገብነቶች አካል ሆነው ሊካሄዱ ይችላሉ። ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት መቆሙን ለማረጋገጥ ሌላ ተከታይ ስብሰባ ወይም ውይይት ከምርመራው በኋላ በኣራተኛው ሳምንት መሸማቀቅ ከደረሰበ(ባ)ት ተማሪ ጋር እና ማሸማቀቅ ካደረሰ(ች)ዉ ተማሪ ጋር ይካሄዳል።

G. አንዳንድ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ሁኔታዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation COB-RA ላይ እንደተገለጸው ከባድ/አሳሳቢ ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፣ አሳሳቢ/አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ማድረግ። ለነዚህ ጉዳዮች፣ በMCPS ደንብ COB-RA የተዘረዘሩት ሂደቶች በት/ቤት ኣስተዳደር/ተወካይ ክትትል እንዲደረግባቸው ያስፈልጋል።

የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ሁኔታ የተማሪ ሪሶርስ መኮንን የሚወስደውን እርምጃ ጨምሮ የፖሊስ እርዳታ ለመጠየቅ አስፈላጊነት ሊኖረው ይችላል፣ ወቅታዊነት እና ለማህበረሰብ የማሳወቅ ሂደቶች ለፖሊስ ምርመራ በሚያመች ሁኔታ መስተካከል ይኖርበታል።

H. የት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት፣ የተማሪ እና ቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት፣ እና የት/ቤት ድጋፍ እና መሻሻል ጽ/ቤት የምርመራ ሁኔታዎችን እና ሪፖርት አቀራረብን የመከታተል እና እነኚህን ሁኔታዎች በተመለከተ ለት/ቤቶች እንደ ግብአት/ሪሶርስ ያገለግላሉ።

I. የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ሁኔታ ውሳኔ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation KLA-RA መሰረት ይግባኝ ፋይል ማድረግ ይቻላል፣ከማህበረሰብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት።

## VI. ስንክልና ላላቸው ተማሪዎች ሂደቶች

A. የማሸማቀቅ አድራጎቶች ወይም አንድ ቅርፀት የተማሪን Free and Appropriate Public Education/ነፃ እና ተገቢ ህዝባዊ ትምህርት (FAPE) በመልሶ መቋቋም አዋጅ ክፍል 504፣ ወይም Individuals with Disabilities Education Act/ስንክልና ያላቸው ግለሰቦች ትምህርት አዋጅ (IDEA) መሰረት ትምህርት መቀበል ላይ ተፅእኖ ያደርግበ(ባ)ት ይሆናል ተብሎ ከታመነበት፣ የሰራተኛ ኣባሎች የIndividualized Education Program/ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ወይም የክፍል 504 ኮሚቴ ስብሰባ ያደርጋሉ።

B. የ(IEP) ቡድን ወይም የክፍል 504 ኮሚቴ የተማሪው/ዋን የ(IEP) ወይም የክፍል 504 ፕላን ድህረ እይታ ያደርግበት እና ለመሸማቀቅ ውጤቶች ምላሽ፣ ካለ፣ በተማሪው/ዋ የFAPE ኣቀባበል ማንኛውም ለውጥ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል።

## VII. ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ስለሚገኝበት ሁኔታ

A. MCPS ቅጽ 230-35፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ፣ በሁሉም ት/ቤቶች በኣስተዳደር ጽ/ቤት፣ የኣማካሪ ጽ/ቤት፣ የሚድያ ማእከል፣ እና በጤና ክፍል መገኘት ኣለበት።

B. MCPS ቅጽ 230-35፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ፣ በMCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

C. የት/ቤት ኣስተዳዳሪዎች የሰራተኛ ኣባሎችን ስለ MCPS ቅጽ 230-35፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ቅጽ፣ መኖር/መገኘት በእያንዳንዱ ኣመት መጀመርያ ላይ ይነግሯቸዋል፣ እና ኣመቱን በሞላ በየወቅቱ ማስታወሻዎች ይሰጣሉ።

D. የት/ቤት ኣስተዳዳሪዎች ተማሪዎችን ስለ MCPS ቅጽ 230-35፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ቅጽ፣ መኖር የትምህርት መጀመርያ ሳምንት ውስጥ በመተዋወቂያ ክፍለ ጊዜዎች፣ እናም ኣመቱን በሞላ በየወቅቱ በማስታወስ ያሳውቋቸዋል።

E. የት/ቤት ኣስተዳዳሪዎች ወላጆችን/ኣሳዳጊዎችን ስለ MCPS ቅጽ 230-35፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ቅጽ፣ መኖር ያሳውቋቸዋል እና የMCPS ማሸማቀቅን በሚመለከት የማህበረሰብ መገልገያዎችና የኢንተርኔት ጣቢያዎች በአመቱ-መጀመርያ ላይ ለተማሪዎችና ለወላጆቻቸው/ኣሳዳጊዎቻቸው በሚላክ መረጃ፣ በት/ቤት ዜና መልእክቶች፣ በስርኣት ኢ-ሜይል፣ እና

የትምህርት ኣመቱ የመጀመርያው Parent Teacher Association/የወላጅ-መምህር ህብረት (PTA) እና የ/ቤት ስብሰባ ወቅት።

F. ት/ቤቱ ኣንድ የተማሪ ወይም የወላጅ/ኣሳዳጊ የመመርያ መፅሃፍ ካለው፣ ስለ MCPS ቅጽ 230-35፣ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ ቅጽ፣ መኖር መረጃ መካተት ኣለበት።

G. የማሸማቀቀ ዘገባውን ቅጽ ተማሪዎች ለማንኛውም የሰራተኛ ኣባል ለእሰመምህር እንዲያደርስ/እንድታደርስ ማቅረብ እንደሚችሉ ይነገራቸዋል። ተማሪዎች የተሞላ የሪፖርት ቅጽ በግል/በአካል ለማቅረብ የሚያሰጋቸው ከሆነ ኣንድ ኣስተማማኝ ሳጥን ውስጥ ለማስገባት እንዲችሉ በት/ቤት ኣስተዳዳሪ በተመረጠ ቦታ ወይም ቦታዎች ይቋቋማል። ኣንድ ት/ቤት አስተማማኝ ሳጥን ካቋቋመ፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች/ኣሳዳጊዎች፣ እና የሥራ ባልደረቦች ሳጥኑ የሚገኝበትን ቦታ እንደሚያውቁ ማረጋገጥ አለበት፣ በየቀኑ ሣጥኑ መታየት/የገባዉ መሰብሰብ እንዳለበትም እርግጠኛ መሆን ይኖርበታል።

## VIII. የድጋፍ ኣገልግሎቶች

መሸማቀቅ ለደረሰበት/ለደረሰባት ተማሪ፣ ማሸማቀቅ ለፈጸመ/ለፈጸመች ተማሪ፣ እና ዳር ተመልካች ተማሪ የሚከተሉት ድጋፎች ይገኛሉ/ይኖራሉ። ዝርዝሩ ሙሉ በሙሉ ባይሸፍንም፣ ት/ቤቶች ከሌሎች ኣቅርቦቶች ወይም ውጤታማ መሆናቸው ከታውቁ ማህበራዊ መገልገያዎች እና ከሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መመርያዎች እና ከMCPS ደንቦች ከሚያከብሩ የተወሰኑ ኣይደለም።

A. የትምህርት ቤት/ስርዓት

1. ትምህርት
2. የመማርያ ክፍል ኣመራር እና የኣነስተኛ ቡድን ምክር ኣሰጣጥ
3. የMCPS "የት/ቤት መገልገያዎች ለወከባ፣ ማስፈራራት እና ለማሸማቀቅ" መመሪያ መፅሃፍ
4. በትብብር የችግር ኣፈታት ዘዴ/የትምህርታዊ ኣስተዳደር ቡድን ሂደት
5. ኣወንታዊ ስነምግባራዊ ጣልቃ-ገብነቶችና ድጋፎች Positive Behavioral Interventions and Supports (PBIS)
6. ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማዎች Functional Behavioral Assessments (FBA)
7. ስነምግባራዊ የጣልቃ መግባት እቅድ Behavioral Intervention Plan (BIP)
8. ሁለገብ የማህበራዊ ክህሎቶች ስልጠና
9. የጠባይ ትምህርት
10. የንዴት/ቁጣ የማብረድ ዘዴ/መታቀብ ስልጠና
11. የማወቅ ስነምግባር ምክር

12. የወላጅ/አሳዳጊ ተሳትፎ

13. የወላጅ/አሳዳጊ ስልጠና/ዎርክሾፕ

14. የእኩያ ድጋፍ ቡድኖች

15. የመርሐግብር መሻሻሎች

16. የት/ቤት መሻሻል እቅድ

17. የተሐድሶ ልምዶች

B. ማህበረሰብ/ቤተሰብ

የመገልገያ ዝርዝር፣ ማሸማቀቅን በሚመለከት የማህበረሰብ መገልገያዎች እና የኢንተርኔት ጣቢያዎች፣ ከት/ቤት ጽ/ቤቶች እና የMCPS ድረ-ገጾች ላይ ይገኛል።

**IX. የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION/ (MSDE) አገናኝ:-**

ዴቦራ ኔልሰን፣ ዶር. Deborah Nelson, Ph.D., NCSP
የክፍል ሃለፊ፣ የት/ቤት ደህንነት እና የሳይኮሎጂ አገልግሎቶች Section Chief, School Safety and Psychological Services
የተማሪ፣ ቤተሰብ እና ት/ቤት ድጋፍ Division of Student, Family and School Support
የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ Maryland State Department of Education
200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201
410-767-0294
Email: Deborah.nelson@maryland.gov

**X. ግምገማ**

ይህ ደንብ ጃኑዋሪ 1/2017 ጀምሮ በየኣምስት ኣመት ይገመገማል።

**የሚዛመዱ ምንጮች:-** Annotated Code of Maryland፣ Education Article፣ §7-424፣ §7-424.1፣ እና §7-424.3.

**ስለ ደንቡ ታሪክ:-** አዲስ ደንብ ጁን 4/2010፣ ኦክቶበር 27/2014 ማሻሻያ ተደረገ፣ ማርች15/2016 ይዘቱ ሳይፋለስ ማሻሻያ ተደርጓል፣ ፌብሯሪ 28/2017 ማሻሻያ ተደርጓል፣ ጁላይ 24/2017 ይዘቱ ሳይፋለስ ማሻሻያ ተደርጓል፣ ማሻሻያ የተደረገበት ጁን 26/2018።